# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)

ሚያዝያ ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ. ም
April 22, 2016

## አትረፍ ያለው በሬ ቆዳው ነጋሪት ይሆናል

ሰሞኑን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃንና በራሱ በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ እንደተረጋገጠው፣ በደቡብ ሱዳን በኩል ድንበር ጥሰው የመጡ ታጣቂዎች በጋምቤላ አካባቢ በሚኖረው ሕዝባችን ላይ እጅግ አሰቃቂ ግድያና ዘረፋ ፈጽመዋል። ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት ስንሰማ የተሰማን ኃዘን መሪር ነው። ኢሕአፓ (አንድነት) ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ወገኖቻችን መጽናናቱን እንዲሰጥልን ይመኛል።

የጋምቤላ አካባቢ ሕዝብ ህወሓት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአገዛዙ ታጣቂዎች ሲቀጠቀጥና በልማት ስም መሬቱን በውጭ ባለሀብቶችና በህወሓት ባለሥልጣናት በመነጠቁ፣ ልጆቹንና ከብቶቹን ይዞ ቀየውን ለቆ ወደ በረሃ በመሰደድ እየተንገላታ ያለ ሕዝብ ነው። መሬታችንን ለቅቀን አንሄድም ብለው የተከራከሩ ገበሬዎችም በአገዛዙ ታጣቂ ኃይሎች የቁም ስቃይ እያዩ ሕይወታቸውን አጥተዋል። አሁንም ለሕዝብና ለሀገር ሉዓላዊነት ደንታ የለሹ መንግሥት ተብየው ጋምቤላ በፌደራል ሥር መሆን አለባት በማለት የአካባቢውን ሚሊሺያ በትኖ ደንበሩን ያለጠባቂ በማስቀረቱ፤ የጎረቤት አገር ታጣቂዎች ድንበራችንን ጥሰው በመግባት ከሁለት መቶ በላይ ወገኖቻችንን ሲገድሉ፣ በመቶ የሚቆጠሩትን አቁስለው በርካታ ሕፃናትንም አፍነው ወስደዋል። በህወሓት/ኢህአዴግ ዘገባ 2000 የቀንድ ከብቶችም እንደተወሰዱ ተነግሯል። የወጣለት መደፈር፣ የነጠረለት ብሔራዊ ውርደት ይኧል ይህ ነው።

ቢያንስ ታፍነው የተወሰዱ ሕፃናት ልጆቻችንን እንኳን ለማስመለስ ህወሓት/ኢህአዴግ የደቡብ ሱዳንን መንግሥት ተጠያቂ ማድረግ ሲገባው፣ የደቡብም ሆነ የሰሜን ሱዳን መንግሥታት በጉዳዩ የሉበትም በማለት የእነሱ ጠበቃ ሆኖ ሲከራከር መሰማቱ እጅግ አሳፋሪ ነው። ሕገ-ወጦች በአንድ አገር ውስጥ ድንበር ጥሰው ወንጀል ሲፈጽሙ

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**
**Phone: 202- 241 2078**
**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ለወንጀለኞች ተጠያቂ መሆን ያለበት ወንጀለኞች የመጡበት አገር መሆኑ እየታወቀ፣ የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ደቡብ ሱዳንን ተጠያቂ ለማድረግ ያልፈለገበት ምክንያት ምናልባት ጭፍጨፋውን ያቀነባበረው እራሱ ህወሓት/ኢ.ህአዴግ ሊሆን ይችል ይሆን? የሚል ሃሳብ ውስጥ ይከተናል። ማን ያውቃል! ህወሓት/ኢ.ህአዴግ እንዲህ ያለ ሤራ መጎንጎን የለመደበት የበርሃ ባህሪው ለመሆኑ የህውዜንን ሕዝብ ገበያ ላይ አስደብድቦ በደርግ ማላከኩ የማይዘነጋ ታሪኩ ነው።

ህወሓት/ኢ.ህአዴግ ለሕዝብና ለሀገር ደንታቢስነቱ የታወቀ ነው። እንኳንስና ገድሎና ዘርፎ የሚሸሽን አሸባሪ ተከታትሎ መያዝና መፋረድ ሊጠበቅበት ቀርቶ ወራሪ ጠላት ቢመጣና አገር ቆርሶ ቢወስድ እንኳን ጉዳዩ እንዳይደለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል ። የአገራችንን ጥፋት የማንሻ የአንድነት ኃይሎች ይህንን እውነታ ተገንዝበን፣ ኃይላችንን አስተባብረን ይህንን ለአገር ሉዓላዊነትና ለሕዝብ አንድነት እንቅፋት የሆነውን የህወሓት/ኢ.ህአዴግን አገዛዝ ማስወገድና ለሕዝባችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማምጣት ይገባናል፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ሀገራችን እየተጓዘችበት ካለው የጥፋት ጎዳና መመለሱ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንና ምንጊዜም መከራ ተለይቶት የማያውቀውን ሕዝባችንን የስቃይ ዘመኑን ማራዘም ይሆናል። ስለዚህ የአንድነት ኃይሎች ጠንካራ ኅብረት ፈጥረንና ትግላችንን አጠናክረን አገር አድን ዘመቻ በማካሄድ ታሪካዊ ግዴታችንና ኃላፊነታችንን እንድንወጣ ኢ.ሕአፓ (አንድነት) ዛሬም ጥሪውን ያቀርባል።

የአገራችን ክብርና ነፃነት በልጆቿ አንድነት ይመለሳል!

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

**Phone:** 202- 241 2078
**Email Address**: eprp-democratic@eprp-ihapa.com